# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን

## የግብርና ታክስ አስተዳደራዊ መቀጫዎችን ለማንሳት የወጣ መመሪያ

## ቁጥር ገባ/10/2004

ሚያዚያ 2004

<u>ባህር ዳር፣</u>

# መመሪያ ቁጥር 10/2004

# በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን የግብርና ታክስ አሰተዳደራዊ መቀጫዎችን ለማንሳት የወጣ መመሪያ

በግብር አስገቢ መ/ቤትና በግብር ከፋዮች መካከል ጤናማ ግንኙነት እንዲፈጠር ማድረግ የግብር አስተዳደር ሥርዓቱን በአስተማማኝ መሠረት ላይ ለማስቀመጥ ከማስቻሉ በተጨማሪ የተሻለ ገቢ መሰብሰብ የሚያስችል በመሆኑ፤

አንዳንድ ግብር ከፋዮች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንዲሁም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሚፈለግባቸውን የግብርና ታክስ ክፍያ በወቅቱ ሳይወጡ የሚቀሩ ግብር ከፋዮች በግብርና ታክስ ህጎች መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣቶች ይጣልባቸዋል እነዚህ ቅጣቶች በመርህ ደረጃ ትክክል ቢሆንም ነገር ግን ከስህተታቸው ተምረው የሚፈለግባቸውን ዋናውን ፍሬ ግብር/ታክስ እንዲከፍሉ በማድረግ አስተዳደራዊ ቅጣቱን እንደ ግብር ከፋዩ ተጨባጭ ሁኔታ ማንሳት ለቀጣይ እነዚህ ግብር ከፋዮች ወደ ህጋዊ ስርዓቱ የሚመጡበት አሰቻይ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያግዝ በመሆኑ፤

አስተዳደራዊ ቅጣቶች ከዋናው ፍሬ ግብርና ታክስ የሚበልጡበት ሁኔታ በመኖሩ ለግብር ከፋዩም ሆነ ለግብር አሰገቢው መ/ቤት ግብሩን ለመክፈልም ሆነ ግብሩን ለመሰብሰብ አሰቸጋሪ ሁኔታዎች እየተፈጠረ ሰለሚገኝ ይህንኑ አሰቸጋሪ ሁኔታ በህግ በመወሰን ችግሩን በመቅረፍ አሰፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በገቢ ግብር አዋጅ 76/94 አንቀጽ 107፣በተ.እ.ታ አዋጅ ማሻሻያ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 14፣በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ማሻሻያ ቁጥር 191/2003 አንቀጽ 20፣በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ማሻሻያ ቁጥር 190/2003 አንቀጽ 17 እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተጨማሪ እሴት ታክስን እንድናሰተዳድር ውክልና በሰጠን መሰረት ለግብር አሰገቢው መስሪያ ቤት አሰተዳደራዊ ቅጣቶችን ማንሳት እንደሚችል በተደነነገው መሠረት እና የክልሉ የገቢዎች ባለስልጣንም እንደገና ለማቋቋም እና ስልጣንና ተግባሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 168/2002 ዓ.ም የታክስ አስተዳደሩን በተመለከተ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን በተሰጠው መሠረት ይህን መመሪያ አዘጋጅቷል።

# ምዕራፍ አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የግብርና ታክስ አስተዳደራዊ መቀጫዎችን ለማንሳት የወጣ መመሪያ ቁጥር ገባ/10/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

**በዚህ መመሪያ ውስጥ**

1. **"ግብር"** ማለት በገቢ ግበር አዋጅ ቁጥር 76/1994 መሠረት የሚከፈል ግብር ነው፤
2. **"ታክስ"** በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994፣ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/1995 ወይም በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 103/1996 መሠረት የሚከፈል ታክስ ነው፤
3. **"አስተዳደራዊ መቀጫ ወይም ቅጣት"** ማለት በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994፣ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/1995 እና በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 103/1996 እና /ወይም የታክስ ግዴታን በአግባቡ ባለመወጣት የሚጣል የገንዘብ መቀጫ፣ የንግድ ፈቃድ የማሳገድ ወይም የማሰረዝ እርምጃ ነው፤ነገር ግን ወለድን አይጨምርም፤
4. **"የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ"** ማለት በገቢ አዋጅ ቁጥር 76/1994 አንቀጽ 105 በተጨማሪ እስት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 40፣ ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 103/1996 አንቀጽ 15 በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/1995 አንቀጽ 18 መሠረት በባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ስር ባሉ ገቢ ጽ/ቤቶች የሚቋቋም ኮሚቴ ሲሆን፣ ከላይ በተገለጹት አዋጆች መሠረት የተጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎች እንዲነሱ የሚቀርቡ አቤተታዎችን በመቀበልና በመመርመር ለገቢ ጽ/ቤት ኃላፊ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ነው፤
5. **"ሐራጅ/ጨረታ"** ማለት የግብር እና /ወይም የታክስ ግዴታን ባለመወጣት የተያዘን ንብረት በግልጽ ወይም በዝግ ሥነ-ስርዓት የመሸጥ ሂደት ነው፤
6. **"የክፍያ ጊዜ ስምምነት"** ማለት ግብር ከፋዩ የግብር፣ የታክስ እና/ወይም ክፍያ ግዴታውን በአንድ ጊዜ ለመፈጸም ሳይቻል ሲቀር ግብር ከፋዩ እና የባለሰልጣን

መስሪያ ቤቱ ክፍያውን የሚፈጽምበትን ጊዜ እና ሁኔታ በተመለከተ የሚያደርጉት ስምምነት ነው።

7. **"የግብር ዘመን"** ማለት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ያለውን ወይም ግብር ከፋዩ ተፈቅዶለት የሚጠቀምበት የአንድ ዓመት የግብር ዘመን ነው፤

8. **"ግብር ከፋይ"** ማለት በግብር፣ በታክስ እና/ወይም አዋጆች መሠረት እንደ ሁኔታው ለገቢ ሰብሳቢ ተቋሙ ግብር፣ ታክስ ወይም ቀረጥ የመክፈል ግዴታ ያለበት ማንኛውም ሰው/ድርጅቶች ነው፤

9. **"ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው"** ማለት በገቢ ግብር አዋጅ 76/94 አንቀጽ 54 መሰረት ግብር ሰብስቦ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሰው/ድርጅቶች ነው፤

10. **"የግብር እና/ወይም ታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ"** ማለት በግብር እና/ወይም በታክስ አዋጆች መሠረት የተዘጋጀና ከግብር ከፋዩ የሚፈለገውን ግብር፣ እና/ወይም ታክስ እንደዚሁም መቀጫ እና/ወይም ወለድ የሚያሳይ በተገቢው ባለስልጣን የተፈረመ ቅጽ፣ ደብዳቤ፣ ወይም ማናቸውም ሰነድ ነው፤

11. **"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት"** ማለት ከፍተኛ የተፈጥሮ አደጋ ወይም ከባድ አደጋ ወይም ግብር ከፋዩ ያለበትን የግብር፣ ታክስ ዕዳ መክፈል እንዳይችል የሚያደርግ ተጨባጭ እና የተረጋገጠ ምክንያት ነው፤

12. **"የግብር፣ ታክስ ዕዳ"** ማለት ለባለስልጣን መ/ቤቱ መከፈል ሲገባው ያልተከፈለ ፍሬ ግብር፣ ታክስ፣ ወለድ እንዲሁም የግብር እና/ወይም ታክስ አስተዳደራዊ መቀጫዎችን ይጨምራል፤

13. **" ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ሆኖ ሕገ-ሰውነት መብት የተሰጠውን ድርጅትንም ያካትታል

14. **"ባለስልጣን"** ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን ነው፤

15. **"የገቢ ሰብሳቢ ተቋም"** ማለት የክልል ገቢዎች ባለስልጣን፣ የዞን አስተዳደር ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ፣ የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት፣የቀበሌ ገቢ መሰብሰቢያ ማእከላትንም ይጨምራል፤

16. በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላት እና ሀረጎች እንደሁኔታው በግብር እና ታክስ አዋጆች ውስጥ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፤

17. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴትም ያገለግላል፤

## 3. የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ እንዲሰበሰቡ በተወሰኑ የግብር፣ ታክስ አይነቶች እንዲሁም በባለስልጣኑ ግብር ከፋዮች እና ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት በተሰጣቸው ሰዎች/ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።ነገር ግን በከተማ አገልግሎት ክፍያ፣በእርሻ ስራ ገቢ ግብር እና ገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

## 4. ዓላማ

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1. ከዋናው ታክስ ወይም ግብር በላይ የሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን በመቀነስ ግብር ከፋዩ ዋናውን ግብር ወይም ታክስ በወቅቱ እንዲከፍል ማድረግ፤
2. በአስተዳደራዊ ቅጣቶች ምክንያት በግብር ከፋዩና በግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን መካከል የሚፈጠሩ ቅራኔዎችን በመፍታት መንግስት ዋናውን ግብር ወይም ታክስ ከነወለዱ በወቅቱ ከግብር ከፋዮች መሰብሰብ እንዲችል በማድረግ በግብር ከፋዩና በግብር ሰብሳቢው መካከል ጤናማና ዘለቄታ ያለው ግንኙነት መፍጠር፤
3. በክልሉ ወጥነት ያለው የግብር አስተዳደር ስርዓት በመፍጠር ግብር ከፋዮች በህግ ተገዥ እንዲሆኑ በማድረግ ልማታዊ ግብር ከፋዮችን ለማበረታታት እና ልማታዊ ያልሆኑትን ወደልማታዊ መስመር እንዲመጡ ለማድረግ፤
4. የግብርና ታክስ አስተዳደራዊ መቀጫዎች የሚነሱበትን አሰራር በህግ በመወሰን በግብር ከፋዮች መካከል ፍትሃዊነት ማስፈን፤

# ምዕራፍ ሁለት

## የግብር እና ታክስ አስተዳደራዊ መቀጫዎች አነሳስ

### 5. ወለድ የማይነሳ ስለመሆኑ

በገቢ ግብር እና በሌሎች የታክስ አዋጆች መሠረት ግብር ወይም ታክስ በወቅቱ ባለመከፈሉ ምክንያት የሚታሰብ ወለድ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚነሳ ወይም ቀሪ የሚደረግ አይሆንም፤

### 6. በግብርና ታክስ ላይ የተጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎች የሚነሱባቸው ሁኔታዎች እና ምጣኔ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ላይ አስተዳደራዊ መቀጫዎች እንደማይነሱ ከተመለከቱባቸው ሁኔታዎች በስተቀር ከዚህ በታች በተጠቀሱት መሠረት በግብርና ታክስ ላይ የተጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊነሱ ይችላሉ፤

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እስከ 5 ከተመለከቱት የግብርና ታክስ አይነቶች እና ግብር ከፋዮች በስተቀር በሌሎች ማናቸውም የግብርና የታክስ አይነቶች እና የግብር ከፋይ ላይ የተጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎች በቀጣዩ ገጽ በቀረበው ሰንጠረዥ 1 ላይ በተመለከተው መስፈርት ምጣኔ መሠረት ሊነሱ ይችላሉ፤

## ሠንጠረዥ 1 - የግብር፣ የታክስ የተጣሉ የአስተዳደራዊ መቀጫዎች አነሳስ መስፈርቶች

| ተ.ቁ | መስፈርቶች | የሚነሳው የመቀጫ መጠን በመቶኛ(%) | | |
|---|---|---|---|---|
| | **የተወሰነው ፍሬ ግብር/ታክስ እና ወለድ የሚከፈልበት ጊዜ** | ግብር ከፋዩ በህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ግብር/ታክስ አስታውቆ የከፈለ ሆኖ | | ግብር ከፋዩ በህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ሳያስታውቅ የቀረ ወይም የዘገየ ከሆነ( የያዘው የሂሳብ መዝገብ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ወይም የሂሳብ መዝገብ/ሠነድ ባለመያዙ ግብር/ታክስ በግምት የተወሰነበትን ይጨምራል |
| | | በልዩነት የተወሰነበት መከፈል ከነበረበት ≤25% በታች ከሆነ | በልዩነት የተወሰነበት መከፈል ከነበረበት 25% በላይ ከሆነ | |
| 1 | ግብር ከፋይ የውሳኔ ማስታወቂያ ደርሶት ወይም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ወይም የግብር ይግባኝ ጉባኤ ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ:-<br>• በዚህ ጊዜ ውስጥ አጠቃሎ ከከፈለ | 100 | 90 | 80 |
| | • ገቢ ጽ/ቤቱ በሚሰጠው እስከ 4ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 90 | 80 | 70 |
| 2 | ግብር ከፋይ የሚፈለግበትን ግብር/ታክስ ወይም ውዝፍ እዳ ባለመክፈሉ ሀብት/ንብረት ተይዞ ለግብር ዕዳው እንደሚውል የሚገልጽ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከመሰጠቱ በፊት ቀርቦ:- | | | |
| | • በዚህ ጊዜ ውስጥ አጠቃሎ ከከፈለ | 90 | 80 | 70 |
| | • ገቢ ጽ/ቤቱ በሚሰጠው እስከ 4 ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 80 | 70 | 60 |

| ተ.ቁ | መስፈርቶች | የሚነሳው የመቀጫ መጠን በመቶኛ(%) | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | ግብር ከፋይ የሚፈልግበትን ግብር/ታክስ ወይም ውዝፍ እዳ ባለመክፈሉ ሀብት/ንብረት ተይዞ ለግብር/ታክስ ዕዳው እንደሚውል የሚገልጽ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ ሆኖም ግን ሀብት ከመያዙ በፊት ቀርቦ:- | | | |
| | • በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 80 | 70 | 60 |
| | • ገቢ ጽ/ቤቱ በሚሰጠው እስከ 4ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| 4 | ግብር ከፋይ የሚፈለግበትን ግብር/ታክስ ወይም ውዝፍ እዳ ባለመክፈሉ ሀብት/ንብረቱን የመያዝ ትዕዛዝ ከደረሰው ወይም ሀብት/ንብረት ከተያዘ በኃላ ሀራጅ/ጨረታ ከመውጣቱ በፊት ወይም በኋላ ቀርቦ፡- | | | |
| | • በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| | • ገቢ ጽ/ቤቱ በሚሰጠው እስከ 4 ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |

2. ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ግብር እና አልፎ አልፎ ንብረት በማከራየት በሚገኝ ገቢ ግብር ላይ የተጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎች፡-

(ሀ) ከዚህ በታች በሰንጠረዥ 2 ላይ በተመለከተው መስፈርትና ምጣኔ መሠረት ይነሳሉ፤

(ለ) ግብር ከፋዩ በህግ ከተወሰነው ጊዜ በኋላም ቀርቦ ግብሩን በማስታወቅ ከከፈለው በዚሁ ሠንጠረዥ በተራ ቁጥር 1 መስፈርትና ምጣኔ መሰረት እንደ ክፍያው ጊዜ መቀጫው እንዲነሳለት ይደረጋል::

## ሠንጠረዥ 2 - ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ግብርና አልፎ አልፎ ንብረት በማከራየት በሚገኝ ገቢ ግብር ላይ የተጣሉ አስተዳደራዊ መቀጮዎች አነሳስ መስፈርቶች

| ተ.ቁ | መስፈርቶች<br>የተወሰነው ፍሬ ግብር/ታክስ እና ወለድ የሚከፈልበት ጊዜ | የሚነሳው የመቀጫ መጠን በ% |
|---|---|---|
| 1 | ግብር ከፋይ የውሳኔ ማስታወቂያ ደርሶት ወይም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ወይም የግብር ይግባኝ ጉባኤ ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ:- | |
| | • በዚህ ጊዜ ውስጥ አጠቃሎ ከከፈለ | 100 |
| | • ገቢ ጽ/ቤቱ በሚሰጠው እስከ 4ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 95 |
| 2 | ግብር ከፋይ የሚፈለግበትን ግብር/ታክስ ወይም ውዝፍ እዳ ባለመክፈሉ ሀብት/ንብረት ተይዞ ለግብር /ታክስ ዕዳው እንደሚውል የሚገልጽ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከመሰጠቱ በፊት ቀርቦ:- | |
| | • በዚህ ጊዜ ውስጥ አጠቃሎ ከከፈለ | 95 |
| | • ገቢ ጽ/ቤቱ በሚሰጠው እስከ 4ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 90 |
| 3 | ግብር ከፋይ የሚፈልግበትን ግብር/ታክስ ወይም ውዝፍ እዳ ባለመክፈሉ ሀብት/ንብረት ተይዞ ለግብር/ታክስ ዕዳው እንደሚውል የሚገልጽ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ ሆኖም ግን ሀብት ከመያዙ በፊት ቀርቦ:- | |
| | • በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 90 |
| | • ገቢ ጽ/ቤቱ በሚሰጠው እስከ 4ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 85 |
| 4 | ግብር ከፋይ የሚፈለግበትን ግብር/ታክስ ወይም ውዝፍ እዳ ባለመክፈሉ ሀብት/ንብረቱን የመያዝ ትዕዛዝ ከደረሰው ወይም ሀብቱ/ንብረቱ ከተያዘ በኋላ በሀራጅ/በጨረታ ከመውጣቱ በፊት ወይም በኋላ ቀርቦ:- | |
| | • በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 85 |
| | • ገቢ ጽ/ቤቱ በሚሰጠው እስከ 4ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 80 |

3. በተ.እ.ታ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 33 ንኡሰ አንቀጽ 1 መሰረት አቅርቦቱን የገዛው ሰው በፈጸመው የማጭበርበር ድርጊት ምክንያት በስህተት አቅርቦቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ወይም በዜሮ ምጣኔ ታክስ እንደሚከፈልበት አድርጎ በወሰደ የታክሱ ተመዝጋቢ ላይ የተጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎች፡-

   (ሀ) ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 2 ላይ በተመለከተው መስፈርትና ምጣኔ መሠረት ይነሳሉ።

   (ለ) የታክሱ ተመዝጋቢ በዚህ በሠንጠረዥ መሠረት ታክሱ የሚነሳለት በህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ታክሱን አስታውቆ ከከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው። በህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ታክሱን ያላስታወቀ እንደሆነ በሠንጠረዥ 1መሠረት መቀጫው እንዲነሳለት ይደረጋል።

4. ለታክሱ ሳይመዘገብ የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ፈፅሞ ታክሱ በግምት በተወሰነበት ግብር ከፋይ ላይ የተጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎች ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 3 ላይ በተመለከተው መስፈርት ምጣኔ መሠረት ይነሳሉ።

## ***ሠንጠረዥ 3 - ለታክሱ ሳይመዘገብ የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ፈፅሞ ታክሱ በግምት በተወሰነበት ግብር ከፋይ ላይ የተጣሉ አስተዳደራዊ መቀጮዎች አነሳስ መስፈርቶች፤***

| ተ.ቁ | መስፈርቶች<br>የተወሰነው ፍሬ ግብር/ታክስ እና ወለድ የሚከፈልበት ጊዜ | የሚነሳው የመቀጫ መጠን (በ%) |
|---|---|---|
| 1 | ግብር ከፋይ የውሳኔ ማስታወቂያ ደርሶት ወይም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ወይም የግብር ይግባኝ ጉባኤ ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ:- | |
| | • በዚህ ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ከከፈለ | 70 |
| | • ገቢ. ጽ/ቤቱ በሚሰጠው እስከ 4ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 60 |
| 2 | ግብር ከፋይ የሚፈለግበትን ግብር/ታክስ ወይም ውዝፍ እዳ ባለመክፈሉ ሀብት/ንብረት ተይዞ ለግብር /ታክስ ዕዳው እንደሚውል የሚገልጽ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከመሰጠቱ በፊት ቀርቦ፡- | |
| | • በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 60 |
| | • ገቢ. ጽ/ቤቱ በሚሰጠው እስከ 4ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 50 |
| 3 | ግብር ከፋይ የሚፈለግበትን ግብር/ታክስ ወይም ውዝፍ እዳ ባለመክፈሉ ሀብት/ንብረቱን ተይዞ ለግብር /ታክስ ዕዳው እንደሚውል የሚገልጽ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኃላ ሆኖም ግን ሀብት ከመያዙ በፊት ቀርቦ፡- | |
| | • በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 50 |
| | • ገቢ. ጽ/ቤቱ በሚሰጠው እስከ 4ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 40 |
| 4 | ግብር ከፋይ የሚፈለግበትን ግብር/ታክስ ወይም ውዝፍ እዳ ባለመክፈሉ ሀብት/ንብረቱን የመያዝ ትዕዛዝ ከደረሰው ወይም ሀብቱ/ንብረቱን ከተያዘ በኋላ በሀራጅ/በጨረታ ከመወጣቱ በፊት ወይም በኋላ ቀርቦ:- | |
| | • በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 40 |
| | • ገቢ. ጽ/ቤቱ በሚሰጠው እስከ 4ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 30 |

5. ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ጋር በተያያዘ ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎች ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 3 ላይ በተመለከተው መስፈርትና ምጣኔ መሠረት ይነሳሉ።

6. አግባብ ባለው የግብርና የታክስ ህግ መሠረት የሂሳብ መዝገብ /ሰነድ እንዲይዝ የሚገደድ ሆኖ ሂሳብ መዝገብ /ሰነድ ባለመያዙ ንግድ ፈቃዱ እንዲታገድበት ውሳኔ የተሰጠው ግብር ከፋይ፣ የሂሳብ መዝገብና ሰነድ ለመያዝ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን አሟልቶ ሲገኝና ይህንንም በቃለ መሃላ ሲያረጋግጥ የንግድ ፈቃዱ ዕገዳ እንዲነሳለት አግባብ ላለው አካል ይፃፍለታል /ማስረጃ ይሰጣል።

## 7. <u>መቀጫዎች ሙሉ በሙሉ የሚነሱባቸው ልዩ ሁኔታዎች</u>

በሠንጠረዥ 1 እና 2 ላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ልዩ ሁኔታዎች መቀጫዎች ሙሉ ለሙሉ ሊነሱ ይችላሉ።

1. ድንገት ደራሽ ችግር ማለትም ድርቅ፣ ተምች፣ የእንስሳት ወረርሽኝ በሽታ፣ መብረቅ፣ ማዕበል፣ጎርፍ፣ ይህን የመሳሰሉት የተፈጥሮ መቅሰፍቶች፣
2. የውጭ ወይም የአገር ውስጥ ጦርነት፣
3. የግብር ከፋይ መሞት፣ ወይም ባልታሰበ ሁኔታ ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ሕመም ሲያጋጥም፣
4. ድርጅቱ በኪሳራ መዘጋቱ በኦዲተር ሲረጋገጥ ወይም በእሳት ቃጠሎ ድርጅቱ መዘጋቱ በመንግስታዊ አካል ሲረጋገጥ፣
5. የስራ ግብር እንዲከፍሉ የሚጠበቅባቸው ተቀጣሪዎች ከስራ ሲቀነሱና ሌላ የገቢ ምንጭ የሌላቸው ሆነው ሲገኙ፣
6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) አፈፃፀም "**ጽኑ ህመም**" ማለት በግብር እና /ወይም ታክስ ማስታዎቂያ ጊዜ ውስጥ ተንቀሳቅሶ መስራት የማያስችልና በታወቀ ህክምና ተቋም/መንግስታዊ እና ህጋዊ ፈቃድ ያለው መንግስታዊ ያልሆነ ህክምና ተቋም/ ቢያንስ በተከታታይ ከ1 /አንድ ወር ላላነሰ ጊዜ የሚያስተኛ ህመም ሆኖ በህክምና ማስረጃ የሚረጋገጥ ሲሆንና በንግድ ስራ እንቅስቃሴውን የሚመራለት ወኪል አለመኖሩ ሲረጋገጥ ነው፡፤
7. በአዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀፅ 94 በተመለከተው መሠረት የገቢ ማስታወቂያው ከመመርመሩ በፊት ግብር ከፋዩ በራሱ ተነሳሽነት ወደ ተሳሳተ የግብር ውሳኔ እና አፈፃፀም ሊያመሩ የሚችሉ ስህተቶችን ያረመ እንደሆነ፣

8. ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ጋር በተያያዘ ግዴታ ተጥሎባቸው ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው አስተዳደራዊ መቀጫዎች የተጣሉባቸው ግብር ከፋዮች ግዴታቸውን ያልተወጡ ከአቅማቸው በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ፣

## 8. መቀጫን የማንሳት ስልጣን

1. የወረዳ/ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት የገቢ አሰባሰብና ክትትል ስራ ሂደት መሪ/አስተባባሪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሠረት መቀጫዎችን ያነሳል፣በየወሩ ሰለቅጣት አነሳስ አፈጻጸም ሪፖርት ለጽ/ቤት ሀላፊው ያቀርባል
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሠረት በልዩ ሁኔታ እንዲነሱ የሚቀርቡ አስተዳደራዊ መቀጫዎችን የገቢ አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት መሪ/አስተባባሪ በሚወስነው ቅጣት አነሳስ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በገቢ ጽ/ቤት የተቋቋመው አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ በመቀበል መርምሮ ለገቢ ጽ/ቤቱ ኃላፊ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል። የገቢ ጽ/ቤት ኃላፊ የውሳኔ ሀሳቡን መርምሮ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መቀጫ እንዲነሳ ያደርጋል።

## 9. የመቀጫ ማንሳት አፈፃፀም

የግብርና ታክስ ግዴታቸውን በተራዘመ ጊዜ እንዲከፈል ለማድረግ ከግብር ከፋዮ ጋር በሚደረግ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ውስጥ ከፍሬ ግብር/ታክስና ወለድ በተጨማሪ የሚነሳው አሰተዳደራዊ መቀጫ ይካተታል። በቀጣይ ግብር ከፋዩ በስምምነት መሠረት ፍሬ ግብሩን/ታክሱንና ወለዱን ከፍሎ ማጠናቀቁ ሲረጋገጥ መቀጫው እንዲነሳ ይደረጋል።

## 10. መቀጫዎች የማይነሱባቸው ሁኔታዎች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 እና 7 በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት አስተዳደራዊ መቀጫዎች እንደሚነሱ የተመለከተ ቢሆንም፡-

1. ግብር/ታክስ ከፋዩ ስለገቢው ምንጭ ወይም መጠን ስለስራው መጠን ወይም ግብር/ታክስ ለመወሰን የሚያስፈልጉ መግለጫዎችን ወይም ሰነዶችን ለማቅረብ እምቢተኛ የሆነ እንደሆነ፣
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 (7) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሃሰት ወይም አሳሳች መረጃ/መግለጫ በማቅረብ የታክስ ባለስልጣኑን ውሳኔ ለማዛባት የሞከረ ወይም እንዲሳሳት ያደረገ እንደሆነ እና በዚህም ምክንያት በወንጀል የተከሰሰና የተፈረደበት እንደሆነ፣እንዲሁም ግብር ከፋዩ ግብር/ታክስ ግዴታውን በማጭበርበር ያልተወጣ መሆኑን የታክስ ባለስልጣኑ የደረሰበት እንደሆነ

3. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በተመለከተው መሠረት ግብር ከፋዩ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ባለማቅረቡ የተጣሉት መቀጫዎች፣
4. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ እንዲያደርግ ግዴታ የተጣለበት ሰው ይህን ግዴታ ባለመፈፀሙ በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 91 (3) እና (4) ላይ በተመለከተው መሠረት የተጣለበት መቀጫ፣
5. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 33 (1) እንደተደነገገው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ከተመዘገበ ሰው የገዛ ማናቸውም ሰው በፈፀመው የማጭበርበር ተግባር ወይም ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ በመቅረቡ ምክንያት የተመዘገበው ሰው በስህተት ግብይቱ ከታክስ ነጻ ወይም በዜሮ ማስከፈያ ልክ እንደሚከፈልበት አድርጎ የወሰደ እንደሆነና የታክሱ ባለስልጣን ወለድ መቀጫውን ጨምሮ ያልተከፈለውን ታክስ ከገዥው ጠይቆ ሲያስከፍል፣
6. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 45 (ለ) እንደተደነገገው ተከፋይ የሚሆነው ታክስ እንዲቀንስ ወይም የሚፈቀደው ተቀናሽ እንዲጨምር የሚያደርግ ሃሰተኛ የሆነ የታክስ ደረሰኝ አዘጋጅቶ ያቀረበ እና የሰበሰበ ወይም የታክስ ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠና ወይም ታክሱንም ያልሰበሰበ መሆኑ ሲደረስበት፣
7. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እንዲጠቀሙ በህግ ግዴታ ተጥሎባቸው ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ለመጠቀም ፈቃደኛ ያልሆኑ ግብር ከፋዮች፣
8. ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ እንዳለባቸው በህግ ወይም በንግድ ዘርፍ ግዴታ የተጣለባቸው ወይም ገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ለታክሱ መመዝገብ እንዳለባቸው በጽሁፍ ያሳወቃቸው ግብር ከፋዮች ለቫቱ ሳይመዘገቡ ከቀሩ፣የተጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎች አይነሱም።

# ምዕራፍ ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**11. የመተባበር ግዴታና የወንጀል ኃላፊነት**

1. ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪየ ለማስፈፀም ስልጣን ከተሰጣቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፤
2. ይህንን መመሪያ የጣሰ ወይም ያሰናከለ አግባብ ባለው ህግ በተደነገገው መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፤

**12. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፤

**13. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደገና በገቢዎች ባለስልጣን ሊሻሻል ይችላል፤

**14. መመሪያው ስራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢዎች ባለስልጣን ከፀደቀበት ከሚያዚያ 01/2004 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

**አስማማው ማሩ**

**ዋና ዳይሬክተር**

ቁጥር____________________

ቀን______________________

## የግብርና  ታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት ማንሻ ቅጽ

የግብር ከፋይ ስም________________________የግ/ከ/መ/ቁ_________________የንግድ ዘርፍ_
_____________ቅጣቱ የሚመለከተው የግብር ዘመን/የሂሳብ ጊዜ_________ቀበሌ____
የቤት ቁጥር___

| ተቁ | የተጣለ/የተወሰነ አስተዳደራዊ ቅጣት ዓይነት | መቀጫ በብር/በሌላ | የተነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት በ%/በሌላ | ቀሪ መክፈል የሚገባው ቅጣት ካለ በብር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

### ቅጣቱን ያነሳው የሥራ ሂደት አስተባባሪ

ስም___________________________________

ቀን____________________________________

ፊርማ__________________________________

# <u>የግብርና ታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲነሳ መጠየቂያ ቅጽ</u>

ለ------------------------------ ወረዳ/ከተማ አሰተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት

-------------------------

**ጉዳዩ:-<u>የተጣለብኝ አሰተዳደራዊ መቀጫ እንዲነሳልኝ ሰለመጠየቅ</u>**

የግብር ከፋይ ስም___________________________________

የግ/ከ/መ/ቁ___________________________

የንግድ_ዘርፍ_________________________________

ቀበሌ________________________________

የቤት ቁጥር____________________________

መቀጫው የሚመለከተው የግብር ዘመን/የሂሳብ ጊዜ _______________

የሚፈለግብኝን ግብር/ታክስ እና ወለድ አጠቃልዩ ከፍዩ ሌሎች አሰተዳደራዊ መቀጫዎች በህጉ መሰረት እንዲነሱልኝ እጠይቃለሁ::

ከሰላምታ ጋር

የአመልካች ስም_____________________________

ቀን___________________________________

ፊርማ________________________________